አንደኛ ዓመት ቍጥር ፫ ።

አዲስ አበባ ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ. ም.

# ዜና፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ዘኢትዮጵያ፡

ይህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዜና ለምእመናን ፣ መንፈሳዊ ምክርን የሚያድል ስለሆነ ዜና ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ተሰየመ ።



| | | |
|---|---|---|
| የድርሳኑ ዋጋ ባገር ውስጥ ባመት ብር 5.00<br>» » » » ያንዱ » 1/2<br>ለውጪ አገር እጥፍ ይሆናል ። | በኢትዮጵያ ቤተ ክህነት<br>ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት<br>ተጠባባቂነት የቆመ | በወር አንድ ጊዜ ይታተማል<br>የፖስታ ሣጥን ቁጥር 1238<br>የቴሌፎን ቍጥር 2047 |



## ስለ ዜና ቤተ ክርስቲያን መቋቋም ።

የዜና ቤተ ክርስቲያን መቋቋም ለጠቃሚነቱ ልዩ ልዩ የትርጓሜ ስልት የሚሰጠው ሲሆን ለጊዜው ለጸሓፊው ሐሳብ በደረሰለት ስሜት መጠን አስተያየቱን ላንባቢዎች መግለጽ አስፈላጊ ሆነ ። ይኸውም በሚገለጽበት ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሁኑ ክፍለ ዘመን ሳይሆን ባለፉት ዘመናት የነበረባትን ኀላፊነትና ድካም ማስታወስ ግድ ሊሆን ነው ።



ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በቤተ መጻሕፍት ውስጥ ።

ኢትዮጵያ መጀመሪያ ሕገ ኦሪትን ፤ ቀጥሎ ሕገ ወንጌልን በየተራ ያለግዳጅ በፈቃዷ ከተቀበለችበት ዘመን ጀምሮ አለፍነው ዘመን ድረስ ምንም አልፎ አልፎ የውስጥ (ሲቢል) ወይም የውጪ ጠላት ወረራ ቢገጥማት የሃይማኖቷ መሠረት የተናወጸበትና ዝንፍ ያለበት ጊዜ አልተገኘም ። እንዲሁ አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉ ፤ መጻሕፍት ሲቈነጻጸሉ የዚሁ አደጋ ከእምነቷ ፈቀ ሊያደርጋት አልሞከረም ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሕገ ኦሪትን ከመቀበሏ ወዲያው ሸምበቆዋን ቀርጣ ፤ ብራናዋን ዳምጣ ፤ ቀለሟን በጥብጣ የውነተኛውን አምላክ ህላዌ ለማስረዳት የምትችልባቸውን ጽሑፎች ማደራጀት ጀመረች ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከሁን ድረስ በየጊዜው የጻፈቻቸው አያሌ ሽሕ መጻሕፍት በየገዳማቱና በያድባራቱ ፤ በየገጠሩና በየሀገሩ ከመገኘታቸው ሌላ በመታሰቢያም ሆነ በሌላ ምክንያት በአውሮፓውያን ‹ሙዚዎም› ቤተ መጻሕፍት መገኘታቸውን በየጊዜው ታሪክ ያወሳዋል ። ያይን ምስክሮች የሆኑ ተመልካቾችም ገልጸውታል ።

ይህንኑም ስትጽፍ ብርዕና ቀለሙ ከሀገሯ ዕፀዋት ፤ ብራናው ከሀገሯ እንስሳት ፤ ጸሓፊው ከሀገሯ ሊቃውንት የተገኙ በመሆናቸው ራሷን ችላ ለራሷ ስለምትሠራ ምንም እንደ ዘመን አመጣሽ መዘውር በቀላል ድካም ለመሥራት ጊዜው ባይሆን ይህ ዓላማዋ ራስን ለመቻል የሚሰጠው ምሳሌ ቀላል አልነበረም ።

www.ethiopianorthodox.org

